# ይድረስ ለ ኣቶ ኣንዳርጋቸው ፅጌ ባሉበት

ሃምሌ 21 2009

በዕለተ እሁድ ሃምሌ 19 እንደ ፈረንጆች ኣቆጣጠር በሚኒያፖሊስ ከተማ ድርጅተዎ ግንቦት ሰባት በጠራው ስብሰባ ላይ ያደረጉትን ንግግር በተለያዩ ድረ-ገጾች ተለጥፎ ኣነበብኩት። ፅሁፉ የእርስዎ ላለመሆኑ ምንም ኣይነት ማስተባበያ ስላልሰጡበት የእርስዎ እንደሆነ እወስደዋለሁ።

መቼም ይህን ፅሁፍ ሲፅፉም ሆነ ለኣድማጮችዎ ሲያነቡ ውስጥዎ ያለውን ጥላቻ እንዴት ኣለሳልሰው እንደሚያቀርቡ ተጨንቀው ሊያቀርቡ እንደሞከሩ መገመት ኣያቅተኝም። የዚህ በተንኮልና በዘረኝነት የተሸረበ ንግግርዎ ኣንድምታ እንደገባኝ ከሆነ ሕወሓትን የሚደግፉ ትግሬዎችን ለማስፈራራት የታቀደ ይመስላል። ሆኖም በስብሰባው ላይ ብዙም ትግሬዎች ካለመኖራቸው ኣንፃር ስገምተው የንግግርዎ ኣላማ ትግሬዎችን ከማስፈራራት ባሻገር የበለጠ ኣላማ እንዳለው መጠርጠር ኣይከፋም። በስብሰባው ላይ የተገኙትን የጉራጌና የሌሎች ብሄረሰብ ኣባላት በትግሬው ላይ የመረረ ቂም እንዲቋጥሩ በሚኩራሩበት የኣማርኛ አፃፃፍ ችሎታዎ ውሸትና እውነታዎችን ኣሰናኝተው ውስጡ ተንኮል ሸክፈው ኣቅርበዋል። እንግዲህ በስብሰባው የተካፈሉ ሰዎች መልዕክትዎን ይቀበሉት ኣይቀበሉት የነሱ ምርጫ ነው።

ትግሬዎችን ለማስፈራራት መሞከርዎን በተመለከተ ግን መልሴ እነሆ።

ኣቶ ኣንዳርጋቸው፤ ኣንድ ተረት ላጫውትዎ። ኣንድ እናት ልጃቸው ጎርምሶ ያስቸግራቸውና ሊቀጡት ኣፈፍ ብለው ሲነሱ ጎረምሳው እንደርስዎ ባለጌ ኖሮ ሴትማ ኣይቀጣኝም እኔ ኮ ወንድ ነኝ ብሎ ለወንድነቱ ማመሳከሪያ ጥብቆውን ፈትቶ ብልቱን ያሳያቸዋል። እናት በዚህ ተበሳጭተውም ሳቃቸውም መጥቶ እንዲህ ይሉታል። “የኔ ልጅ እሱንማ በፈራን ኣንተም ባልተወለድክ”።

ኣቶ ኣንዳርጋቸው እንደርስዎና ጓደኛዎ ያላችሁትን ውሽልሽሎች በፈራን ኖሮ ደርግም ባልወደቀ እርስዎም እንዲህ ብልግናዎን ገሃድ ለማውጣት ባልተገደዱ ነበር።

ትግሬዎች እንደቀደምት ኣባቶቻችን ከፍርሃት ይልቅ ጀግንነት፣ ከጥላቻ ይልቅ ፍቅር፣ ከልዩነት ይልቅ ኣንድነትን የምንወድ መሆናችንን አስረግጨ ልነግረዎ እፈልጋለሁ። ሕወሓት ከጭቆና ነፃ ያወጣቸው  ድርጅት ስለሆነም ብዙ ትግሬዎች ቢደግፉት ኣይግረምዎ። ለወደፊቱም ቢሆን ሕወሓትን የምንደግፈውም ሆነ የምንቃወመው በተለመደው ርቱእና ምክኒያታዊ በሆነ ምዘናችን እንጂ እንደርስዎ ያሉ ውሽልሽል የተንኮል ኣንቀልቦች በሚነዙብን ማስፈራሪያ ተደናግጠንና በፍርሓት ተሸብበን እንዳልሆነ ይወቁት።


ቴዎድሮስ ሳልሳዊ

tewodros_salsawi@yahoo.com

ካለሁበት